


ለእኔ ያለው ዓላማ



Word from the Word
በ ዴሪክ ፕሪንስ

ዴሪክ ፕሪንስ ነኝ፤ ከቃሉ ለእናንተ የሚሆን መልዕክት ይዤላችሁ ቀርቤአለሁ።

> እግዚአብሔር ብድራትን ይመልስልኛል አቤቱ፥ ምሕረትህ ለዘላለም ነው፤ አቤቱ፥ የእጅህን ሥራ ቸል አትበል። መዝሙር 138:8

እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን ዓላማ እንዳለው ማወቅ መልካም ነው። በዚያ ያለው ቅዱስ ቃል ጌታ የእኔን ዓላማ ይፈጽማል አይልም፤ ይልቁንም ጌታ ለእኔ ያለውን የእርሱን ዓላማ ይፈጽማል ነው የሚለው። ትልቅ ልዩነት አለ። እኔ አንድ ዓላማ ሊኖረኝ ይችላል፤ እግዚአብሔር ደግሞ ሌላ ሊኖረው ይችላል። እግዚአብሔር የእኔን ዓላማ እንደሚፈጽም ዋስትና አይሰጥም፣ ነገር ግን የእርሱን ዓላማ እንደሚፈጽም ቃል ይገባል።

በመቀጠልም መዝሙረኛው እንዲህ ይላል፦ “አቤቱ፥ ፍቅርህ [ይህም ማለት ‘ቃል ኪዳንን የሚጠብቅ ታማኝነትህ’ ማለት ነው] ለዘላለም ይኖራል።” እግዚአብሔር ዓላማውን በሕይወታችን ውስጥ ለመፈጸም ራሱን ለእኛ ሲሰጥ፣ ያ ለአሁንም ሆነ ለዘላለም የሆነ ቁርጠኝነት ነው።

ከዚያም ምናልባት ከተስፋ መቁረጥ ስሜት የተነሳ መዝሙረኛው፣ “የእጅህን ሥራዎች አትተው” ይላል። በአንድ ወቅት በካንሰር በሽታ ምክንያት የሞት አፋፍ ላይ የነበረች አንዲት ጠንካራ አማኝ ሴት አጠገብ የነበርኩበትን ጊዜ አስታውሳለሁ። እሷም ያንን የመጨረሻ ቁጥር “ዘ ሊቪንግ ባይብል” በተባለው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም እንዲህ ስትል አነበበችው፦ “አንተ ፈጥረኸኛል፤ አትተወኝ።” እነዚህን ቃላት ስታነብም ታላቅ መተማመን ነበራት። “አንተ ፈጥረኸኛል፤ አትተወኝ።” ነገር ግን ይህ ለእያንዳንዳችን የሚሆን እውነት ነው። እግዚአብሔር ፈጥሮናል፤ እርሱ አይተወንም። እርሱ ዓላማ አለው፤ያንን ዓላማ ደግሞ ይፈጽመዋል። ምናልባት ያ የእናንተ ዓላማ ላይሆን ይችላል፣ነገር ግን የእርሱ ዓላማ ይሆናል። ምንም ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ብታልፉ ያ ዓላማ የጸና እና የማይናወጥ ሆኖ ይቆማል።

መንፈሳዊ ጽሑፍ ★

ግልባጭ: WD-WFTW-126-AMH

መጨረሻ የዘመነው: 28 Oct 2026

ድህረገፅ: Derekprince.com/am/resources

